JW.ORG

# ማኑሄ

የመጽሐፍ ቅዱስ ካርድ
39

## ማኑሄ



### ጥያቄ

**ሀ.** ለማኑሄ ሚስት የተገለጠላት መልአክ እንደተናገረው ሳምሶን እስራኤላውያንን ከእነማን እጅ ያድናል?—መሳፍንት 13:5

**ለ.** ማኑሄ እንዲህ ሲል ጸልዮአል:- “ልከኸው የነበረው ያ የእውነተኛው አምላክ ሰው እንደገና ወደ እኛ ይምጣና _____ ይስጠን።”—መሳፍንት 13:8

**ሐ.** እውነት ወይስ ሐሰት? ማኑሄ ለመልአኩ ምግብ አዘጋጅቶለት ነበር።—መሳፍንት 13:15, 16, 19









## ማ ኑ ሄ

**አጭር የሕይወት ታሪክ**:- የመስፍኑ ሳምሶን አባት። አንድ መልአክ ለማኑሄ ሚስት ወንድ ልጅ እንደምትወልድ ነገራት፤ በዚህ ወቅት ማኑሄ ሳምሶንን እንዴት ማሳደግ እንደሚችሉ መመሪያ ለማግኘት ይሖዋን በጸሎት ጠየቀ። “እውነተኛው አምላክ የማኑሄን ቃል ሰማ”፤ ከዚያም መልአኩ ለማኑሄ ሚስት የሰጣትን መመሪያ በድጋሚ ለማኑሄ ነገረው። መመሪያው ናዝራዊ ልጃቸውን እንዴት ማሳደግ እንደሚችሉ የሚገልጽ ነበር።—መሳፍንት 13:8-14

### መልስ

**ሀ.** ከፍልስጤማውያን።

**ለ.** መመሪያ።

**ሐ.** ሐሰት። ለይሖዋ የሚቃጠል መባ አቅርቧል።




www.jw.org/am © 2016 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania